# 8 ትምህርት እና ስልጠና

ዩኬ

በዩኬ ውስጥ ጥገኝነት ጠያቂዎች ብዙውን ጊዜ ትምህርት የማግኘት መብት አላቸው። መማር አይችሉም የሚል ሰነድ ከተሰጠዎት ስህተት ሊሆን ይችላልና የህግ ምክር መጠየቅ አለብዎት። ሁሉም ጥገኝነት ጠያቂዎች ነፃ የእንግሊዝኛ ትምህርት የማግኘት መብት አላቸው።

## እንግሊዝኛ መማር

በዩኬ ውስጥ፣ እንግሊዝኛን ለመማር ወይም ለማሻሻል እንዲረዳዎ ትምህርት የመማር መብት አለዎት። አብዛኛውን ጊዜ እነዚህ ክፍሎች “እንግሊዝኛ ለሌሎች ቋንቋ ተናጋሪዎች” ወይም “ESOL” ይባላሉ።

ወደ ዩኬ ሲመጡ የESOL ትምህርት መማር ከፈለጉ ለአካባቢዎ ኮሌጅ ማመልከት አለብዎት። አንዳንድ ጊዜ ኮሌጆች የጥገኝነት ጥያቄያቸው ውሳኔ እስኪያገኝ ድረስ ቢያንስ ለ6 ወራት እየተጠባበቁ ካልሆነ አዲስ ተማሪዎችን አይቀበሉም።

መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ የቤተ ክርስቲያን ቡድኖች እና ሌሎች የማህበረሰብ ድርጅቶች ለጥገኝነት ጠያቂዎች ነፃ የእንግሊዝኛ ትምህርት ሊሰጡ ይችላሉ። በሆቴልዎ ውስጥ ያሉ ሌሎች ሰዎችን መጠየቅ ወይም የሚከተለውን በመስመር ላይ መፈለግ ይችላሉ፦ ‘ነጻ የእንግሊዝኛ ትምህርቶች’ + (የከተማዎ ስም)።

## ለተጨማሪ ስልጠና ወደ ዩኒቨርሲቲ ወይም ኮሌጅ መግባት

ጥገኝነት ጠያቂዎች ከፈለጉ ዩኬ ውስጥ ዩኒቨርሲቲ የመግባት መብት አላቸው።

ዩኒቨርሲቲ ለመግባት ማመልከቻ መሙላት እና ተቀባይነት ማግኘት አለብዎት። አንዳንድ ማመልከቻዎች በጣም አስቸጋሪ ናቸው፣ እናም እርስዎ አስቀድሞ ዲግሪ ወይም ሌላ የትምህርት ደረጃ ያስፈልግዎት ይሆናል።

እንግሊዝ እና ዌልስ ውስጥ ዩኒቨርሲቲ መግባት ብዙ ጊዜ ነፃ አይደለም፣ እና ብዙ ሰዎች ክፍያ መክፈል አለባቸው። በስኮትላንድ አንዳንድ ሰዎች መክፈል የለባቸውም። ዩንቨርስቲ ሲገቡ የኑሮ ወጪዎንም መክፈል አለብዎት። ይህ እንደሚገቡበት ዩኒቨርሲቲ ሁኔታ ውድ ሊሆን ይችላል።

እንደ ጥገኝነት ጠያቂ በዩንቨርስቲ ለመማር ካመለከቱ በጣም ውድ የሆኑ አለም አቀፍ ክፍያዎች ሊያስከፍሉዎት ይችላሉ። እንደ ጥገኝነት ጠያቂ ለትምህርት ክፍያ እና ለኑሮ ወጪዎች ለመክፈል የሚረዱ የመንግስት ብድሮችን ማግኘት አይችሉም። እንደ ስደተኛ ወይም የሰብአዊ ጥበቃ ያለው ሰው ካመለከቱ፣ እንደ ዩኬ ተማሪ ተመሳሳይ ክፍያ እንዲከፍሉ እና በተመሳሳይ መንገድ የመንግስት ብድር ማግኘት ይችላሉ።

ለጥገኝነት ጠያቂዎች እና ለስደተኞች (የስደተኛ ሁኔታ ወይም የሰብአዊ ጥበቃ) አንዳንድ ነጻ የትምህርት እድሎች አሉ ለበለጠ መረጃ ይህን አገናኝ ማየት ይችላሉ፦
https://star-network.org.uk/access-to-university/scholarships/list/
https://www.displacedstudent.org.uk/

የስደተኛ ትምህርት ዩኬ ወደ ኮሌጅ ወይም ዩኒቨርሲቲ ለማመልከት ምክር ለመስጠት የ1፡1 ክፍለ ጊዜዎችን ይሰጣል https://www.reuk.org/helpforcollege

## በዩኬ ውስጥ የእርስዎን የትምህርት ደረጃዎች መጠቀም

በዩናይትድ ኪንግደም ውስጥ፣ በአብዛኛው ያለዎትን ማንኛውንም ዲግሪ ወይም ሌላ የትምህርት ደረጃ መጠቀም ይችላሉ። የትምህርት ደረጃዎን እንዳገኙበት ቦታ ሁኔታ ለ"ንፅፅር መግለጫ" ማመልከት ሊኖርብዎ ይችላል። ይህ የርስዎ ዲግሪ ወይም የትምህርት ደረጃ በዩኬ ውስጥ ከተመሳሳይ ዲግሪ ወይም የትምህርት ደረጃ ጋር ተመሳሳይ ወይም በተቀራራቢ ደረጃ ተመሳሳይ መሆኑን የሚያሳይ ህጋዊ ማረጋገጫ ነው። ለንፅፅር መግለጫ መክፈል አለቦት። በአሁኑ ጊዜ ዋጋው £60 አካባቢ ነው። የምስክር ወረቀቶችዎ በእንግሊዘኛ ካልሆኑ ሰነዶቹ መተርጎም አለባቸው እና https://www.ecctis.com/ ን ማነጋገር እና የተተረጎሙ የምስክር ወረቀቶችዎን መላክ ይኖርብዎታል እናም እነሱ የንፅፅር መግለጫውን ይልኩልዎታል። እንዲሁም በክፍያዎች ላይ እገዛ ለማግኘት https://www.ruthhaymantrust.org.uk/grants ን ይመልከቱ።

# 8 ትምህርት እና ስልጠና

ዩኬ

ከ18 ዓመት በታች የሆኑ ጥገኝነት ጠያቂዎች በዩኬ ውስጥ የተለያዩ የመማር መብቶች አሏቸው። ሁሉም ልጆች በዩኬ ውስጥ ትምህርት የመማር መብት አላቸው። ይህ ስደተኞች የሆኑ ወይም ጥገኝነት የሚጠይቁ ልጆችን ይጨምራል።

## ትምህርት መማር

በዩናይትድ ኪንግደም ከ 5 አመት ጀምሮ እስከ 16 አመት ድረስ ያሉ ሁሉም ልጆች በትምህርት ላይ መሆን አለባቸው። ሁሉም ልጆች እስከ 16 አመት ድረስ ትምህርት መማር አለባቸው። ከዚያም 18 ዓመት እስኪሞላቸው ድረስ በትምህርት ቤት ለመቆየት ወይም ተግባራዊ ክህሎቶችን ለመማር መምረጥ ይችላሉ። ትምህርት ቤቶች በአካባቢው ባለስልጣናት የሚተዳደሩ እና ለመማር ነፃ ናቸው።

የማህበራዊ ጉዳይ ሰራተኛ ወይም የጉዳይ አስፈጻሚ ካለዎት ለትምህርት ቤቶች በማመልከት እንዲረዱዎት መጠየቅ ይችላሉ። ከ18 ዓመት በታች የሆኑ ልጆች ያሉዎት ወላጅ ከሆኑ፣ በተቻለዎት ፍጥነት ወደ ማረፊያዎ አቅራቢያ በሚገኝ ትምህርት ቤት ማስመዝገብ አለብዎት። የአካባቢዎን ምክር ቤት ስም ይፈልጉ + ለትምህርት ቤት በመስመር ላይ ይመዝገቡ።

## ትምህርት ቤት ስገባ ምን ልጠብቅ?

በመጀመሪያዎቹ ጥቂት ሳምንታት ውስጥ የትምህርት ቤት ሰራተኞች እና አስተማሪዎች ይረዱዎታል። ሰላምታ ይሰጡዎታል እና ከትምህርት ስርዓቱ ጋር ያስተዋውቁዎታል እናም እርስዎ መማር እንዲችሉ፣ በትምህርት ቤት ጥሩ ስሜት እንዲሰማዎት እና ምናልባት የሚያጋጥሙዎትን ተግዳሮቶች - ለምሳሌ ከቋንቋ ጋር የተያያዙ ችግሮች ላይ እንዲረዱዎት ምን እንደሚያስፈልግዎ ይመለከታሉ።

አዲስ ትምህርት ቤት መግባት ለእርስዎ ቀላል ላይሆን ይችላል። ነገር ግን በትምህርት ቤት ሰራተኞች እና በማህበራዊ ጉዳይ ሰራተኛ እንደሚደገፉ እርግጠኛ ይሁኑ፣ እና የትምህርት አመትዎን ለመጀመር የሚያስፈልጉዎት ነገር ሁሉ እንዳሎት ማረጋገጥ አለባቸው። ስለ ስሜቶችዎ ለአስተማሪዎች ወይም ለማህበራዊ ጉዳይ ሰራተኛ ለመናገር አይፍሩ እና አስቸጋሪ በሆነበት በማንኛውም ነገር ይረዱዎታል።

## ከ16 እስከ 18 ዓመት የሆኑ ወጣቶች

በአከባቢዎ በኮሌጅ የሚሰጠውን የ ESOL ትምህርቶች መማር ይችላሉ። በሳምንት ለ18 ሰአታት እንግሊዝኛ ይማራሉ እና ሌሎች ኮርሶችንም ሊማሩ ይችላሉ። የሚያስተምሯቸውን ኮርሶች በተመለከተ መረጃ ለማግኘት የኮሌጆችዎን ድር-ጣቢያዎች ማየት ይችላሉ እንዲሁም ክፍት ቀን - መማር ስለሚፈልጉት ኮርስ የበለጠ ለማወቅ እና መስፈርቶች ወይም የትምህርት ደረጃዎች የሚያስፈልጉዎት ከሆነ ለመመልከት የሚችሉበት ቀን ሄደው መሳተፍ ይችላሉ።

## የአዋቂዎች ESOL ክፍሎችን የት ማግኘት እችላለሁ?

ለESOL ትምትህርት በአቅራቢያዎ ካለ ኮሌጅ መመዝገብ ይችላሉ፣ ነገር ግን 'ESOL የመስመር ላይ ትምህርቶች'ን የሚያቀርቡ የተለያዩ ድርጅቶችም አሉ እና ከቤት ሆነው መከታተል ይችላሉ። ለምሳሌ እነዚህን ድርጅቶች ማነጋገር ይችላሉ፡-

www.babelsblessing.org
cityofsanctuary.org
conversationsoverboreders.org (የመስመር ላይ ትምህርቶች ከበጎ ፈቃደኞች አስተማሪዎች)

እንዲሁም፣ በአካባቢዎ የሚገኘውን የስደተኛ ድጋፍ ሰጪ ድርጅት ማነጋገር ይችላሉ እና የESOL ትምህርትን እንዲመዘገቡ ሊረዱዎት ይችላሉ።

Refugee Legal Support